# ሞት አይቀር!



ለምንስ መወለድ፣ ለምን መፈጠር!
በዓለም ተቀላቅሎ ብልህና ደንቆሮ
አንበሳና ዝሆን፣ ጦጣና፣ ዝንጀሮ፣
የዚህ ዓለም ዕብደት ለቅሶና እሮሮ፣
መቸም አያበቃ ቢነገር፣ ቢነገር...
ሞት አይቀር፣ ሞት አይቀር!



መወለድ ለከንቱ፣ አጉል መፈጠር!
በዕብደቱ ወጥመድ አምላክን ማመን፣
በጭንቀት ተጠብቦ፤ "ጌታ አደራህን፣
ከጥፋት አድነኝ!" ብሎ መለመን፣
ልብ ያጽናናል እንጂ ከሞት አያድን...
ሞት አይቀር፣ ሞት አይቀር!



የሕይወት ትርጉሙ ሳይገባኝ ስኖር፣
ራሴን እያጽናናሁ ጭንቄን ሳቃልል፣
ሆድ ሲያውቅ "ዶሮ ማታ!" ብየ ሳታልል፣
በሰማይ ቤት አለኝ እያልኩ ስዋልል፣
ዶሮው ይቅርና፣ ሽሮውስ የታል?
ሞት አይቀር፣ ሞት አይቀር!

ገ/ኢ. ጐርፉ።